## የCOLUMBIA (ኮሎምቢያ) ግዛት የህዝብ ቤተመጽሀፍት
## መቀጮዎች እና ቅጣቶች

---

### መነሻ ታሪክ

የDC የህዝብ ቤተመጽሀፍት ተገለጋይ ተኮር፣ፍትሃዊ፣ እና ለሁሉም ክፍት ለመሆን ይጥራል። ነገር ግን መቀጮዎች ቤተመጽሀፍቱ አስቀድሞም ሊያገለግላቸው ለሚሰራው የህብረተሰብ ክፍል-አነስተኛ ገቢ ያላቸው ነሪዎች- ተደራሽ እንዳይሆን እንቅፋት ይፈጥራል እናም የቤተመጽሀፍት ሰነዶች በወቅቱ እንዲመለሱ የሚያበረታቱ ውጤታማ መሳርያ አይደሉም።

የመዘግየት መቀጮዎችን መሰረዝ ኢፍትሀዊነትን ለማስወገድ እና በጣም ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ተደራሽነትን ለማሻሻል ይረዳል። ቤተመጽሀፉ የባለአደራ ቦርዱ ዘግይተው ለተመለሱ የቤተመጽሀፍ ሰነዶች የመዘግየት መቀጮዎች መጣልን እና መሰብሰብን ለማስቀረት እንዲመርጡ ይመከራል። በ2015 ቦርዱ የወጣት አካውንቶች (እድሜያቸው 19 እና ከዚያ በታች) ላይ ብቻ መቀጮዎች እና ክፍያዎች እንዲቀሩ መርጧል።

ቤተ መጽሀፉ በተጨማሪ አዋቂዎች ለጠፉ ወይም ለተጎዱ ሰነዶች እና እቃ የምትክ ክፍያዎችን ማስከፈሉን እንዲቀጥል ይመከራል።

### አዲስ የፖሊሲ ቋንቋ

የDC የህዝብ ቤተመጽሀፍት መተካት ያለባቸውን ሰነዶች እና እቃዎችን ይመረምራል እና ክፍያዎች ይሰበስባል። እቃዎች ጉዳት ደርሶባቸው ሲመለሱ ምትክ ሊያስፈልግ ይችላል። የውሃ ጉዳት እና/ወይም የጎደሉ ክፍሎች ጨምሮ ጉዳትሌሎችን ሊያካትት ይችላል። የተለመደ ማርጀት እና መቀደድ ይጠበቃል እና ጉዳት የደረሰባቸው እቃዎች የመመዘኛ መስፈርት ውስጥ አይካተትም። የተለመደ ማርጀት እና መቀደድ ማለት ሊቀደዱ የደረሱ ወረቀቶች፣ ሊቀደዱ የደረሱ የመጽሀፍ ሽፋኖች ወይም መለበጃዎች፣ እና የጎደለ የሚዲያ ስእል ሽፋንን ሊያካትት ይችላል።

### የምትክ ክፍያዎች፣

- ጠንካራ ሽፋን ያላቸው መጽሀፍት - $20.00 እያንዳንዱ
- ስስ ሽፋን ያላቸው መጽሀፍት - $15.00 እያንዳንዱ
- ሲዲዎች እና ዲቪዲዎች - $15.00 እያንዳንዱ

ከአርባ ዶላር ($40) በላይ የምትክ ክፍያ ያለባቸው አዋቂዎች (እድሜያቸው 20 እና ከዚያ በላይ) ክፍያዎቹ እስኪከፈሉ ወይም እቃዎቹ እስኪመለሱ ድረስ የመበደር መብታቸው ይታገዳል።

የቤተመጽሀፍት ሰራተኛው ወይም ተወካይ በራሱ/ሷ ፍቅድ ስልጣን የቤተመጽሀፍ እቃዎች የምትክ ክፍያዎችን ሊተዉ ይችላሉ። ይህ አማራጭ ተበዳሪው የሚከተሉትን ምክንያቶች ሲያቀርቡ አገልግሎት ላይ ሊውል ይችላል፣ ሆስፒታል መተኛት፣ የቤተሰብ ሞት፣ እስራት፣ የእሳት ቃጠሎ፣ ጎርፍ፣ ወይም ሌላ የግል ከባድ ችግር።

የቤተመጻህፍት ሰራተኛው ወይም ተወካይ ተበዳሪው የቤተመጽሀፉ እቃ ጉዳት ሳይደርስበት እንደተመለሰ ሲገልጹ እና ቤተመጽሀፉ ውስጥ ሲገኝ ወይም ቤተመጽሀፉ በድንገተኛ ምክንያት ዝግ ከነበረ የምትክ ክፍያዎቹን የመሰረዝ ስልጣን አላቸው።

በቤተመጽሀፉ የባለአደራ ቦርድ ጸድቋል
ሜይ 14፣2020